# <u>ደግሞም ግልፅ ደብዳቤ ለፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም</u>

ከዳግማዊ አደፍርስ

# <u>ተስተማረና ተጣፊ</u>

"'Father Antony always preaches to us about being strong in the face of opperession. "Never give in or br a coward against the occupation," he says. But I saw him forced to strip down to his undergarments at a check point one day! Where was his courage then? .... 'His chest hair was white! I couldn't bear to see him like that. ...... With his chest hair curling in the wind for the soldiers to laugh at! How many times have I told you, the grown-ups are no use? They can't protect us or themselves.' " ***Qouted from the book – where the streets had a name; by Randa Abdel-Fattah; Sydney 2008 page 68-69.***

"You don't just write a book; you have to live it first." የራሴው አባባል

*መፅሓፍ ዝም ብለው ከመሬት ተነስተው እንዲያው በግድየለሽነት፤ በማንአለብኝነትና በማንአህሎኝነት እንፃፍህ ብለው የሚያካሂዱት የአጉራ ዘለል ስራ መሆን የለበትም። በቅድሚያ መሟላት ያለባቸውና የግድ የሚሉ ጉዳዮች አሉ። ከነዚህም ጉዳዮች አንዱና ዋነኛው የሚፅፉትን ታሪክ መኖርና ያንኑ ደግሞ በኃላፊነት ስሜት ለመወጣት መፃፍ ነው።*

*በተለይ የአገርን፤ የሕዝብንና የተከታታይ ትውልዶችን ታሪክ መዝግቦ ለመጪ ትውልዶች ለማቆየት የህዝቡን ኑሮ መኖርን፤ ከክፋትና ከቂም-በቀል የፀዳ አዕምሮንና ልቦናን ማዳበር የግድ ይጠይቃል። ይህም ማለት የአገርንና የትውልድን ታሪክ እንዳለ፤ እንዳለ ባይሆንም ከዕውነቱ በፍፁም ባላፈነገጠ ሁኔታ  በታሪክ ቀመስ ልብ-ወልድ መልክ እንኳ ለማቅረብ በመጀመሪያ በቦታው መገኘት ብቻ ሳይሆን የባለታሪኩን ሕዝብ ኑሮ መኖርን ይጠይቃል። በአካል፤ በህሊና፤ በዕውቀትና በምርምር አብሮ መኖርን! ዝም ብለው ስለሞነጫጨሩት መፅሓፍ የመማሪያና የማስተማሪያ ክቡር እሴት ሊሆን አይበቃም፤ አይችልምም። እውነቱ በሀሰት ተለውሶ ወይም ብዙ ሐሰትና ቅጥፈት በስስ እውነት ተቀባብቶ፤ መፅሃፉ ሲጀምር የነበረው ፍሬ ሃሳብ መሃል ላይ ወይም ወደማብቂያው ላይ ጠፍቶና ከሌላ ሃሳብ ጋር ተምታትቶ ሲደመደም የሆነ ችግር አለማለት ነው።*

*አገራችን ኢትዮጵያ ደግሞ ጥሩ ትጉህና ደፋር ፀሐፍት ነበሯት። ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል፤ አቤ ጉበኛ "አልወለድም"ን፤ "ሞቻአለሁኝ"ንና ሌሎቹን ብርቅ መፃህፍቱን ሲፅፍ፤  አዲስ ዓለማየሁ "ፍቅር እስከ መቃብርን" ሲፅፉ፤ ብርሃኑ ዘሪሁን የአብዮት ዋዜማን ማግስትንና ሌሎችን መፅሃፍቶቾን ሲፅፍ፤ ይልማ ሀብተየስ እነዓለምፀሓይ ወዳጆ የተጫወቱበትን "ያልተከፈለ ዕዳ" የተሰኘውን ቲያትራዊ ድርሰት ሲፅፍ፤ የዛሬን አያድርገውና ጌታቸው አብዲ "ጓድ ለጓዱ ጓድ ቢሆንም ጓድ ለጓዱ ጓድ ሊሆን … አይችልም" የሚለውን ትኩረት-ሳቢ ሐረግ ያካተተበትን ቲያትራዊ ድርሰት ሲፅፍ፤ ወዘተ ወዘተ ኖረውት ነው። ሎሬት ፀጋዬ ገ/መድህን ግጥሞቹንና ቲያትሮቹን ሲፅፍና ሲያደራጅ፤ ኃይሉ ገሞራው ሲፅፍ፤ ሲገጥምና ሲቀኝ፤ ደብተራው ፀጋዬ ገብረመድሕንና ሌሎች የዴሞክራሲያ አዘጋጅ ቦርድ አባላት ሲፅፉ ኖረውት ነው። ማንነትን ላለማግነን ስል ብቻ ሳላነሳቸው የማልፋቸው በሕይወት ያሉ ፀሐፊዎች አገራችን አሁንም እንዳሏት እግረመንገዴን አንስቼ ልለፍ። የሚያስፈልገው ዓይንን ገለለጥ ማድረግና ከራስ ባሻገር ማየት መቻል ነው።*

ይህን ግልፅ ደብዳቤ እንድፅፍ ያስገደደኝ፤ ብዙ- በጣም ብዙ- እንቢልታ የተነፋለትና ብዙ ከበሮ የተደለቀለት አዳፍኔ በተሰኘ ርዕስ የፃፍከውን መፅሐፍ ተብሎ ነገርን ማንበቤ ነው። ባለን የዕድሜ ልዩነት ምክንያት ኢትዮጵያዊ ጨዋነትን መሰረት አድርጌ "አንቱ" እያልኩኝ ልፅፍልህ ጀምሬ ነበር። የ እኔ አንቱታ የሚመነጨው ከአንገት በላይ ከከንፈር ላይ የሚነፍስ ሳይሆን ከውስጥ ከአንጀቴ የሚፈልቅ ነውና ለአንተ ሲሆን እምቢ ስላለ በአንተታ ላስኪደው ተገደድኩ። ወደድኩም።

 ከዚህ በፊት ባማሪኛም ሆነ በእንግሊዝኛ ከጻፋቸው መጻሕፍት ውስጥ የተወሰኑትን ያነበብኩ በመሆኔ የተነሳና፤ የጽሕፈት ሥራህ መነሻና መዳረሻው ያንን የታገለ ትውልድ መራገም መሆኑን ስለማውቅ ቁም ነገር አገኝበታለሁ ከሚል ሳይሆን፤ ከበሮ ደላቂዎቹን ለመታዘብ ስል ነው ያነበብኩት። መጽሐፉን ማንበቤን ጀምሬ እስከምጨርሰው ድረስ የተረዳሁትም  ከካቻምና አምና፤ ከአምና ዘንድሮ ምንም ያልተለወጥክ መሆኑንና ለከርሞም የማትለወጥ መሆንህን ነው። አዲስና የተለየ ንድፈ-ሃሳብ ልታመነጭ ያልቻልክ ያንኑ እጅ እጅ ያለ ትውልድ የመሳደብ ተግባር ላይ የተሰጠህን ሚና መጫወትህን ብቻ ነው የታዘብኩት።  ያው እኒያንን ሁለት አስከፊ ሥርዓቶች ታግሎና አይከፍሉ ውድ ዋጋ ከፍሎ ያስወገደና ሦስተኛውን ከፉ ሥርዓት እየታገለ ያለ ትውልድን መራገም፤ ማጥላላትና ማቆሸሽ የዘወትር ተግባርህን የከለስክበት እንጂ ምንም አዲስ ነገር የሌለበት ፍሬ ከርስኪ መሆኑን ነው የተገነዘብኩት። እግረመንገዴንም ከበሮ ደላቂዎቹንና የአይጥ ምሥክር ድንቢጥ ዓይነት አዳናቂዎችንም ታዘብኳቸው። አንዳንዱን ትዝብቴንም ወደኋላ ላይ አመላክትኃለሁ። ልቀጥል።

ሰፊውን የዚህን መፅሐፍና የአንተን የፀሓፊውን ስነ ልቦና ግምገማና ትችት ለመጪ ትውልዶች ልተውና እኔ ለጊዜው ከላይ ከላዩ ነካ ነካ አድርጌ ብቻ ልተወው። ይህን የማደርገውም ይህ ደብዳቤዬ ግልፅና ያልታሸገ በመሆኑ ሌሎች አንባቢዎች አሉትና አንባቢዎቼን ያለ አግባቡ ላለማሰላቸትና ውድ ጊዜያቸውን ላለማባከን ነው። ብዙ አዳፍኔን ሲያነቡ የባከነ ወይም የሚባክን ጊዜ አለና! በዚያ ላይ ደግሞ ገና መጪ ትውልዶች መፅሐፉን አንብበውና በጊዜያቱ ከነበሩት ሓቆች ጋር አገናዝበው የመመርመር ሥራውን ከእኔ በተሻለ ሁኔታ ይወጡታል ብዬ ስለማምንም ነው።

ለእኔ አገርንና ታሪክን ተረካቢ የሚሆን መጪ ትውልድ አለ። ያ መጪ ትውልድ ደግሞ የባህል፤ የታሪክና የሁሉም ነገር ግንዛቤው ከቀደሙት ትውልዶች የበለጠና የዳበረ ነው የሚሆነው ብዬ የማስብና የምቀበል ሰው ነኝ። ለእኔ መጪ ትውልድ የሚነሳውና ዕውቀቱን የሚገነባው ከምንም ከባዶ አይደለም። ከርሱ በፊት የነበሩትና የቀደሙት ትውልዶች በጣሉለት የታሪክና የባህል መሰረት ላይ ስለሆነ ዕውቀቱ የሚገነባው መጪ ትውልድ ሁሌም የተሻለ ነው፤ ምንም ያህል አደናቋሪና አደናቃፊዎች ብትበዙበትም። አዎ ምንም - ያህል አደናቃፊ ጋሬጣዎች ቢደነቀሩበትም የተሻለ ዜጋ ይሆናል ብዬ የማምንም ነኝ። አንዳንዱ ሰው ግን ከርሱ ከራሱ መሞትና ማለፍ በኋላ ምንም ቀጥሎ የሚመጣ ነገር ያለ አይመስውለም። ስለሆነም ቀቢፀ-ተስፋ ያጠቃዋል። ያንኑ የራሱን ቀቢፀ- ተስፋ ደግሞ ለሌሎች ሊያስተላልፍና ሊያጋባ ሲማስን ይገኛል።

ይኸው ከእኛ ሞት በኋላ "ምንም ነገር የለም" የሚለው ቀቢፀ-ተስፋ ነው አንተንና መሰል ዶክተር ፕሮፌሰሮችን አሁን የምትሉትንና፤ እየሆናችሁ ያላችሁትን ዓይነት ሁኔታ እንድትሆኑ እያደረጋችሁ ያለው። ምን ማለቴ እንደሆነ ላሳይ!

የሸገር ኤፍ ኤም የቅዳሜ ጭውውት አቅራቢ  በቁልምጫ "ፕሮ" እያለች - "ከሞቱ በኋላ እንደምን ሊታወሱ ይፈልጋሉ" - ብላ ብትጠይቅህ ለዚህ ከፍተኛ ቁምነገርን ለያዘ ጥያቄ የሰጠኸው መልስ በጣም

አስገራሚ ነበር -አስጸያፊም። "እኔ ከሞትኩ በኋላ ታሰብኩ አልታሰብኩ እኔ ምን አገባኝ" የሚል ነበር። (ዩ ቱብ ላይ ሔዶ ይህን ማግኘት ይቻላልና እኔ " ምላሴ ላይ ፀጉር ይብቀል፤ ከምላሴ ፀጉር ይነቀል" ዓይነቱ ጮርቃ መሓላ መደርደርና መወራጨት አያስፈልገኝም)

እንደምን ያለ አሳፋሪና አስተዛዛቢ መልስ ነው??

ይህ ዓይነቱ መልስ " እኔ ከሞትኩ በኋላ ሰርዶ ቢበቅል ባይበቅል ምን አገባኝ?" ከሚለው አባባል የሚለይበትን አንዳች ምክንያት የሚነግረኝ ይኖር ይሆን?? አይጠፉምና እነማን እንደሆኑ ወረድ ብዬ አመላክትቻለሁ። እነርሱም ከሞቱ በኋላ ትውልድም - ምንም ነገር - የለማ!!

አምባገነኖችና አርጋጅ አሽርጋጆቻቸው ሌላኛዎቹ የዚሁ የቀቢፀ-ተስፋ ስነልቦና ተጋሪዎችና አራጋቢዎች ናቸው። በመፅሐፍህ ውስጥ ሥልጣናቸውን በትውልድ ወይም በዘር ሐረግ አገኙት ብለህ የምትከራከርላቸውአፄና ከነሂርማን ኮህን ጋር ተመሳጥረህ ወደ ሓራሬ የሸኘኸውፈርጣጩ ኮሎኔል ዋነኛዎቹ ምሳሌዎች ናቸው። አፄው "እኔ ከሞትኩ ወይ ዘውዴ ከተናጋ፤ ምድር ከፍ - ሰማይ ደግሞ ፀሐይንና ጨረቃን እንደያዘች ዝቅ ይላሉ። ከዚያ በኋላ እንኳን መጪ ትውልድ አሁን ያለኸውም አበቃልህ" ብለውና በአጫፋሪዎቻቸውና በውጪ የጥቅም ተጋሪዎቻቸው ይኸንኑ አስብለው ሊያደነቁሩን ሲሞክሩ ከረሙብን ። ያ እነመንግሥቱና ግርማሜ ንዋይ እንዲሁም እነዋለልኝ መኮንንና እነማርታ መብራቱን የተከተለው ትውልድ ደርሶ አሻፈረኝ እስኪል ድረስ "ዕድሜ ለርሳቸው" እያስባሉ ህዝብን ለርሃብ ዕርዛትና ለደዌ ዳርገውት ኖሩ። መሓይሙ ኮሎኔልም በጊዜው ለተነሳ ማንኛውም አስተዳደራዊ ፖለቲካ፤ ምጣኔ ሀብታዊና ማኅበረሰባዊ ጥያቄ ሁሉ ጦርነትና ሽብር መፍትሔ እየመሰለው በፍርጠጣ ሓራሬ እስኪገባ ድረስ "ያለ-እኔ ኢትዮጵያ የምትባል አገርህን አታገኛትምና የማደርግህን ሁሉ ባደርግህ እሺ ብለህ ተገዛ እንጂ ... እኔ ከሌለሁ አገርም ምንም አትኖርህም" እያለና አጫፋሪዎቹም "እውነቱን ነው እርሱ ከሌለ አገር ይፈርሳል እያሉ" ስንቱን ዜጋ ለጦርነት እየማገዱትና ሽብርን እያስፋፉ ኖሩ።

ነገርን ነገር ያመጣዋል ሆነና የአምባገነኖቹን ጉዳይ አነሳሁት እንጂ ዋናው ጉዳዬ ከአዳፍኔና ከአንተ ከደራሲው እንዲሁም ከአጨብጫቢዎቹ ጋር ነውና ወደዚያው ላምራ።

አድፍኔ ገፅ 12 ላይ ልውሰድህና እስኪ የፃፍከውን ረጋ ብለህ አንብበው። ያ እነግርማሜ ንዋይን እነዋለልኝ መኮንን የሚያራግም አብዜ በጣም ወደኋላ ወስዶህ ያስረግምህ ገባ። እኛ እንደአገርና እንደሕዝብ አለን የምንለውን ታሪክና ቅርስ ማራከስና ማዳፈን የተልዕኮ መነሻና መዳረሻ ነውና አሁን ደሞ ተንጠራርተህ የመተማው ሰማዕትን አፄ ዮሐንስን ማራከስ ላይ ገባህ። ያለምንም ህፍረት በአገር ክህደት ውንጀላ ጀመርካቸው። ለዚህ አሳፋሪና አስነዋሪ ውንጀላ ደግሞ በምስክርነት የተጠሩት አንድ ሀጋይ ኤርሊክ የተባለ የውጭ ሀገር ፀሓፊና አቶ ተክለፃዲቅ መኩሪያ ናቸው። የውጭ ሀገሩን ፀሐፊ ለምሥክርነት በጠቀስክበት ፍጥነት እዚያው በዚያው "አስተሳሰቡ የተምታታበት ..." ብለህ ማስረጃህን እንክትክቱን ስለምታወጣው እኔ የምለው አይኖረኝም።

ውንጀላህን ያጠናከረልህ መስሎህ ግን "አቶ ተክለፃዲቅ የሚከተለውን ይላሉ" ብለህ ያቀረብከው በደንብ ያልተረጋገጠ ማስረጃ ላይ ላተኩር።

*"ከዶጋሊው ጦርነት ወዲህ የጦር ጠቅላይ አዛዥነቱን ንጉሠ ነገሥቱ ከራስ አሉላ አንስተው ለታላቅ ወንድም ልጃቸው ለራስ ኃይለማሪያም ሰጥተው አሉላን በሐማሴን ግዛት ስለወሰዷቸው ቅሬታ ነበራቸው **<u>ይባላል</u>**። "* (መስመርና ማጉላት የእኔ)

ይባላል??????? ወይ ይባላል!!! በዚህ አሁን በተደረሰበት የዕውቀትና የምርምር ደረጃ የዚህ "ይባላል" ተብሎ የተፃፈን ታሪክ እንደ ማመሳከሪያ መቅረብ ዳርዳሩ ካልገባችሁ ብዙ እንዳንራራቅ ትንሽ ልበል። ባጭሩ መሰሪና አደገኛ የሆነ የክፍፍል ሥራ ነውና ዝም ተብሎ መታለፍ የለበትም።

ግድ የለም አቶ ተክለፃዲቅ ያንን ታሪክ በፃፉበት ጊዜ የተደረሰበቱ የዕውቀትና የምርምር ገደብ ነበረባቸውና "ይባላል" ብለው ታሪክን በስማ በለው ፃፉት እንበል። እንዴት አሁን በተደረሰበት የመረጃ ብቃት ዘመን ሊቁ ምሁር ተመራማሪ ፕሮፌሰር ተብዬ እንዲህ ያደርጋል? አሁን ባለን የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሁኔታ የዚህ ዓይነቱ አተራረክ የሚጠቅመው ለነማን ነው? ለወያኔና አጃቢዎቹ ብቻ ነው እንጂ። ምክንያቱም ተልዕኮውም ግቡም ወያኔያዊ ነው። ኢትዮጵያዊያንን በመንደር በዘር መከፋፈል ነው።

"የኢትዮጵያ ህዝቦች አብረው መታገልና ዴሞክራሲና እኩልነት የሰፈነበትን ሥርዓት በጋራ መስርተው በአንድነት መኖር አይችሉምና ተገነጣጠለው የየራሳቸውን መንግሥት መመስረት አለባቸው" አልነበር ወያኔ የሚለው? የቱ ጋ ነው ልዩነታችሁ የኛ ተመራማሪ ፕሮፌሰር??

ሥራህ የትግራይን ወገኖቼን ከጎንደር ወገኖቼ ያፈራቅቃል። ያራርቃል። በተመራማሪ ተብዬው ህሊና ውስጥ ክህደቱ የተደረገው በአፄ ቴዎድሮስ ላይ ነበርና። ለትውልድ ሊስተላልፍ የተፈለገውም ይኸንኑ ነው። ወይኔ ወገኖቼ! ወያኔ ይከፋፍላል፤ ሰውየው የበለጠ የክፍፍል ምክንያትና መሣሪያ ያቀብላል። እንዲህ ነው ሲረዳዱ የከረሙብን። ወያኔ በሰላምና በመረጋጋት መገዛት ይላል፤ ሰውዬ የሌለውን መላ እየመከረና "ወያኔ ቢገድልም ቢያስርና ቢያፈናቅልም እናንተ ይቅርታ ጠይቁ" ይለናል።

እዚያው ገፅ 12 ላይ አዳፍኔ የሚከተለውን ጽፈሃል። "የሸዋው ንጉሥ ምንሊክ በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል የሚያገባው አልነበርም"። አረ ባክህ?? ያልታደለ ጆሮ አይሰማው ነገር የለም። ይህ ደግሞ ከየት የተገኘ ዕውቀት ነው? የትኛው ሊቅስ ይሆን ደግሞ ለዚህ ዓይነቱ እብደት እንደዋቢ የሚጠራብን? መሰሪና ጥራዝ ነጠቁ መለስ ዜናዊ ይሆን? ይህ አንተ ልጄ ትለው የነበረ ሕሙም "ምንሊክ የኮሎኒያሊስቶቹን የአፍሪካ መቀራመት እኩል ተዋግቶ

ድርሻውን ያገኘ ነበርና ኮሎኒአሊስት ሆኖ ሊመደብ ይገባዋል" ብሎ አንድ ሰሞን ጉድ! አሸኝቶኝ ነበረ። ከርሱስ ተፈጥሮ በቸርነቷ ገላገለችን።

የተማረ የተመራመረ ሰው ቁጥብ ነው። እንኳን የራሱ ህዝብ ባህል ቋንቋና ታሪክ የሌላውን ያከብራል። የራሱንም መታረም ያለበትን በአግባቡ እንዲታረም እያሳሰበ በጎ በጎውን ይከላከላል - በጥርሱም በጥፍሩም። አንተ ግን ለዚህ አላደለህምና አድፍኔህ ውስጥ - "ቅኔ የመከሸፍ ምልክት ነው" ብለህ አረፍከውና አስቆዘምከኝ። "አረ ለመሆኑ የእንግሊዞቹ ኢዲየም" ምንድን ነው ብዬ ብጠይቅህ - እሱ የሥልጣኔ ምልክት ነዋ!" የምትል መሆንህን አንተነትህን በቅጡ የሚያውቅ ሁሉ ምሥክር ይሆነኛል። ኢ*_የት!

አጉል ሙገሳ ያወፈፈው መግደል ባይሆንለት ያስገድላል። መፍጀት ባይሆንለት ያስፈጃል። ጠቁሞ ያስይዝና ያስገርፋል። በአጭሩ ይሁዳነትን ደግሞ ደጋግሞ ይሠራል። ሲወርድ ደግሞ ስድብ ሙያው ይሆናል። የዘፈን ዳር ዳሩ እስክስታ ነውና ዋለልኝንና ያን ትውልድ ለመስደብ እነአስቴር አወቀን እነ እጅጋየሁ ሽባባውን መንደርደርያ አደረካቸው። "እነዚህ ስደተኞች የትም ተሰድደው 'ሀገር ሀገር የሀገር ብርቁ' እያሉ ያላዝናሉ" ስትል ወረድክባቸው። እዚያው አዳፍኔ ውስጥ!

ባያድለን ነው እንጂ አሁን እንዲህ ያለው ቃል በዚህ ዕድሜ ላይ ሆኖ (ግማሽ አካል አፈር ሆኖ ባለበት) ካልታበደ በቀር ከጤነኛ ሰው አንደበት የሚወጣ ነው? ለነገሩማ “መታፈር በከንፈር” የሚለውም ብሂል ለአንተ የከሸፈ ነው። ልጨምር።

ለስድብ ዋሺንግተን ድረስ (ሌላም ተልእኮ ነበረህ!) ተንደርድረህ ሄደህ "አሸቱ ጮሌንና ያን ወሎዬውን አስጠርቼ ... " ያልከበትን የድምፅ ቅጂ አዳምጬ - "ወይ ፕሮፌሰር! ዛሬም አልተሻለህም?" እያልኩና እየተገረምኩ አዳፍኔን ማንበብ ቀጠልኩ።

ያ ደደቢት ያደደበው ክርፍፍ፤ ዜግነትን ደረጃ አበጅቶለት "ከኢትዮጵያዊነት በፊት ትግራዋይ ነኝ"፤ ሲል የነበረና እንደምንም ተንፏቆ ትሪፖሊ የደረሰ ጊዜ ደግሞ "እኛ ዓረቦች ነን፤ ካላመንከኝ ዜናዊ የሚለውን ስሜን ተመልከት ምንጩ የመን ነው"፤ እንዲሁም በውጭና በአገር በቀል ባንዳዎች (አንተኑ ጨምሮ) ተደግፎ ደግሞ ሥልጣን ላይ ሲወጣ "ኢትዮጵያዊነት ተደራድሬና ፈልጌ የምቀበለው እንጂ ..." እያለ የቆጥ የባጡን ሲቀባጥር የነበረን ቅዠታም ኢትዮጵያዊነት አንገትህን ሰጥተህ የምትከራከርበት ሀቅ ሆኖ ሲታይህ የዋለልኝ መኮንን ኢትዮጵያዊነት ግን ተንሸዋረረብህና “ወሎዬው” ብለህ ስትል ሰማሁህና ታዘብኩህ። አይ ዕድሜ ጠገብነት! አይ ተመራማሪነት! አይ ፍርድ አወቅነት!

ያ ይሁን ግድየለም። እረ ለመሆኑ ማንና ማንን ነው አስጠርተህ ያነጋገርከው? ምታወራው ሌላ፤ የምትፅፍው ደግሞ ሌላ። መፅሐፍ የተባለው ነገር ገፅ 259 ላይ የሚለው እንዲህ

ነው። "ዓመቱን ባላስታውሰውም በዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ በነበርንበት ዘመን ብርሃነመስቀልንና ዋለለኝ (ስታወራ ግን እሸቱ ጮሌንና ዋለልኝ) ጠርቼ አነጋግሬአቸው ነበር ..."። አረ ለመሆኑ ሰዎቹን ታስታውሳቸዋለህ? ወይስ ኢህአፓና ያን ትውልድ የመስደብ ተልዕኮህን ያሳካህ በመሰለህ ቦታና ጊዜ ሁሉ አንዱን ከአንዱ እያምታታህ ማቅረብ ስለማይገድህ ነው? ወይስ እድሜ ተጫነህና መርሳት እየበረከተ ነው? ጉዳዩን በጥሞና ላሰበው ሰው ሐቁ ያ ይመስለኛል። ወይ መካሪ ጠፍቶአል አሊያም አንተ አትሰማም። እዚህ ላይ ምን ማለቴ እንደሆነ ለመረዳት የሚከተሉትን አምስት ዓረፍተ ነገሮች ልብ ብለህ ተመልከትና መርምር። በ2003 ዓ ም "የክህደት ቁልቁለት" ብለህ ካሳተምከው መፅሀፍ ላይ የተገኘ ነው።

"በወያኔ ጨቅላ አስተሳሰብ አንድነት ሁለት ዓይነት ነው። አንደኛው የፊውዳል አስተሳሰብ አዝማሪዎች የሚላቸው የሚያራምዱት ኢትዮጵያ **የግዛት አንድነት** ነው። ሌላው **"የሕዝቦች አንድነት"** የሚሉት ነው። ግዛት ማለት መሬቱ ከሆነ ‹ህዝቦች ከተባሉት ጋር እንዴት ነው እንዲህ ተለይቶ በቅራኔ ሊቆም የቻለው? የግዛት አንድነት 'መጥፎ ሲሆን ፣የህዝቦች አንድነት ጥሩ ሊሆን የሚችለው እንዴት ነው? ...**የዜግነት አንድነት የሕዝብ አንድነት** መሆኑን መገንዘብ እንዴት ፊውዳል ...ያሰኛል" (ገፅ 37)

ምኑ ከምን ጋር እየተነፃፀረ ነው እዚህ ጋ እየቀረበ ያለው?

**የግዛት አንድነት "የሕዝቦች አንድነት" የዜግነት አንድነት የሕዝብ አንድነት**

የተያያዘ አንድ ሃሳብን በአምስት ዓረፍተ ነገሮች እንኳ መግለፅ እየተቸገርክ ነው ያለኸው ማለቴ ነው።

እንዲያው ተነስተው - ***እውነት እውቀት እምነት - እውቀት እምነት እውነት - እምነት እውነት እውቀት - አሊያም - ሀሰት ክሽፈት ክህደት - ክሽፈት ክህደት ሀሰት - ክህደት ሀሰት ክሽፈት*** - እያሉ ቃላትንና ዓረፍተ ነገሮችን እየደጋገሙና እያገላበጡ ቢፅፉት ምንም ጥቅም የለውም። እንዲያውም አነሰ ከተባለ ትዝብት ላይ ይጥላል፤ ሲበዛ ደግሞ ያስከስሣል። አዳፍኔ መፅሐፍ ሊባልና ለገበያ መቅረብ አይገባውም ነበር።

ለምን? በለኝ። አንደኛ መፅሐፉ ቀደም ሲል ከፃፍካቸው ነገሮች የተለየ ይዞ የመጣው ምንም አዲስ ነገር የለውም። ሌላውና ዋናው ጉዳይ የአዳፍኔ ጠርቀም ያለ ክፍል (ከገፅ 165 - 208) ከአሁን ቀደም ባቀረብካቸውና አንባቢዎች በፅሁፎችህ ላይ የሰጡትን ትችቶች ያካተተ ነው። እነዚህን በሌሎች ሰዎች የቀረቡ ትችቶች በመፅሐፍ መልክ ጠርዘህ ለገበያ ማቅረብ በሌላ ቢሆን አገር የሚያስከሥሥ ወንጀል ነው። ባያስከሥሥም ያስነቅፋል። እነተስፋዬ ሀፒሶ ሲነቀፉ ሰምተን ነበርና። አንተንማ ማን ነቅፎህ? እንዲያውም ከበሮ ይደለቅልሃል እንጂ። ይህም ዓይነቱ የተስተካከለ የጎሊና ዳኝነት

ጉድለት ነው አንተን ልቅና ትውልድን ተሳዳቢ ያደረገህ። ገና - ያኔ ገና - በቅርቡ ታግሎ የተሰዋውን ትውልድ መሳደብ በጀመርክ ጊዜ ተው ተብለህ ተመክረህ ቢሆን ኖሮ በጣም ተንጠራርተህ የአፄ ዮሐንስን ሰማዕትነት አታክቸለችልም ነበር። በዕንቁላሉ በተቀጣህ ጥሩ ነበር።

ስለሰማዕቶቻችን ጉዳይ ከተነሳ ሺህ ጊዜ ብትክድ ብትክድ፤ ልትክድ ያልቻልከው የአቡነ ጴጥሮስን ብቻ ነው። ግን እርሳቸውንም ቢሆን እጅግ በጣም አርቀህና ከደመና ሁሉ በላይ አሳልፈህ ታስቀምጥና በቅርብ እንዳናያቸው ታደርጋለህ። አንድ ነገር ብዬ ልለፍ። እኛ ግን የትናንቱንም ሆነ የዛሬ ሰማዕቶቻችንን በአጠቃላይ ከነአፄ ዮሐንስና ከዚያም በፊት ጀምረን፤ በነዋለልኝና ማርታ አድርገን እነደብተራውና ጓዶቹን አውስተን፤ የቅርቦቹንም እነዳሮ ነጋሽና ሽብሬ ደሳለኝ ፤ ዕምቦቃቅላዎቻችንን ደብሬን ባቢሌንና ነቢዩን (አረ ስንቱን) እነ ነጂብን እነ ውልጫፎን እነአብድራህማንን እነአቸናፊና ብርሃኑ ዘለቀን እነቆፍጣኖቹን አንዳርጌ ብዙነህን ሁሉንም ከልባችን አናቅራቸውም። ልጆቻችንን የልጅ ልጆቻችንን በነሱ እንሰይማለን። ቲያትራዊ ድርሰቶችን እንፅፍላቸዋለን፤ ሲኒማ እንሰራላቸዋለን (ለአንተም የመሰሪ ባህሪህን ቦታ አናሳጣህም። ከዚህ ፅሑፍ መጀመሪያ ላይ ከ ራንዳ አብደልፋታህ መፅሐፍ ገፅ 68-69 የወሰድኩት - የምላስ ተዋጊ የተግባር ተንብርካኪ "ፋዘር አንቶኒ" ዓይነት ገፀ ባህሪ!)። ገና ድምፃችንን ከፍ አድርገን እንዘምርላቸዋለን። እስከዚያው ግን በዝምታችን እናወድሳቸዋለን።

አንተ ግን ጣትህን ወደሌሎች ከመጠቆም በቀር ለምታደርሳቸው ጥፋቶች ፀፀት ተሰምቶህ ንሥሃ የምትገባው ነገር የለህም። አንድ እኔም አንተም የምናውቀው ነገር ላንሳልህ። ደርግ አጣሪ ኮሚሽን አቋቁሞ አንተንና ዶ/ር በረከት ሀብተሥላሴን የኮሚሺኑ ሊቀመናብርት አድርጎ ሰይሞ የአፄውን ዘመን ባለሥልጣናት "ኑና ታስራችሁ ተመርመሩ" ብሎ ሲጋብዝ፤

1. ራስ መስፍን ስለሺ

2. ብ/ጄኔራል ሙሉጌታ ወ/ዮሐንስ

3. ራስ ፀሐዬ እንቁሥላሴና ሁለት ወንድሞቻቸው (ታደሰና ወርቁ)

"ወይድ" ብለውት ወደየሚሄዱበት ሂደው ሳይመጡ ይቀራሉ። እናንት የመርማሪ ኮሚሽን አባላት ለደርጉ "በ24 ሰዓት ጊዜ ውስጥ መጥታችሁ እጅ ካልሰጥችሁ ቋሚም ሆነ ተንቀሳቃሽ ንብረታችሁ ይወረሳል ብለህ አውጅ ብላችሁ" መከራችሁ፤ አዋጁም ታወጀ። ራስ መስፍን ስለሺ ከጅማ፤ ብ/ጀኔራል ሙሉጌታ ወልደዮሐንስ ከዝዋይ ተመልሰው ለዕስራት፤ እንግልትና ግድያ ተዳረጉ። ደርጉ ቤተሰብና ቤተዘመድ ምሬቱን በኃዘን ዕርሙን በእንባ ተራጭቶ እንዳያወጣ ከለከለ። ዘብ በየደጃፋቸው አቆመ። እኔ የቆሙትን ዘቦች ተጋፍቼ ብ/ጄነራል ሙሉጌታ ቤት ደርሼ ያገኘሁአቸውን የቤተሰብ አባላት አፅናንቼ ወጣሁ፤ የመጣው ይምጣ ብዬ። አንተ ግን ...!

አሁን ዓይንህን በጨው ታጥበህ፤ አዛኝ ቅቤ አንጓች ሆነህ፤ "ራስ አበበ አረጋይንና ራስ መስፍን ስለሺ የገደላችሁ" ብለህ መፃፍህ አንሶ አሜሪካ ለአሜሪካ እየዞርክ የኢትዮጵያ ሕዝብን በስድብ ትሞልጫለህ። ያገኘኸው አድማጭም በይሉኝታ ይሁን በሌላ ሲያጨበጭብልህ ከረመ። አንተ ደግሞ እንደማንኛውም ራስ ወዳድና አምባገነን ጭብጨባ ትወዳለህና ደግመህ ደጋግመህ አልከው። ልቀጥል!

ማንም ሰው ለህሊናዊም ሆነ ህጋዊ ፍርድ የምስክርነት ቃል ለመስጠት ምስክርነትን ከሚሰጥበት ጉዳይ ጋር በተያያዘ የተፈፀመውን ሁኔታ ከቦታውና ጊዜው ጋር አያያዞ፤ በወቅቱ የነበሩ ሰዎችን ቢቻል በስም በዕድሜ በፆታ እየለየ ማቅረብ ይጠየቃል። አለበለዚያ የምስክርነት ቃሉ ተቀባይነትን አያገኝም። ፕሮፌሰርም ቢሆን! አንት ግን ስሙን እንኳን በቅጡ የማታውቀውን ወይም ለማወቅ እንኳን ቅንጣት ያህል ሳትጨነቅ “የመድኃኔአለም ት/ቤት ዲሬክተርን "(ፈቃደ ?)" ኢህአፓ ገደለው” ትላለህ። ኢህአፓን እስከወነጀልና እስካጠቆረ ድረስ ለአንተ ህሊናም ህግም የፍርድ ሥርዓትም ሥፍራ የላቸውም። በዚህ ጉዳይ ላይ አንድ ነገር ብዬ ልለፍ። ኢትዮጵያና ህዝቧ እንዲህ እንደሆኑ አይቀሩም። የህግ የበላይነት የሚሰፍንበት፤ ፍትህ የሚሟላበት ቀን ይመጣል። ያኔ ኢህአፓ እንኳን ይቅር ብሎ ቢተውህ እኔ በማትኖርበት ለፍርድ አቀርብሃለሁ።

እስከዚያው ግን አንተ መድረክና አድማጭ ከተገኘ ሌላው ቀርቶ ደርግ - በተለይም ቡከኑ ኮሎኔል - ቆሻሻ ሥራውን እንዲሠሩለት እያደረገ ከተጠቀመባቸው በኋላ የገደላቸውን የአራት ኪሎውን አረመኔ ዕብድ ግርማ ከበደን የገደለው፤ እንዲሁም ትንሽ ገንዘብ የነበራቸውን (እንደነ የጨው በረንዳ ባለቤት የነበሩትን አባ ቦራን፤ የአዲስ ከተማ ቡና ቤት ባለቤት አቶ ከተማ ብሩን፤ የነፃነት ጎህ ሆቴል ባለቤትን (አረ ስንቱን እጥቅሰዋለሁ?)) ለገንዘባቸው ሲል ብቻ እንደነፍቃዱ አስቻለው ዓይነቱን ያዲስ አበባ ገዳይ የከፍተኛ የአብዮት ጥበቃ አባላትን አስተባብሮ ምስኪኖቹን ሌሊት ከቤታቸው እያወጣ የፈጃቸውን አረመኔ ሻለቃ ብርሃኑ ከነደን የገደለውም ኢህአፓ ነው እያልክ ለፍፍ። ዘንድሮ መድረኩም ተገኝቶአልና በምድረ አሜሪካ የዘጠኝ/አስራአንድን የሽብር ተግባርን የፈፀሙትን ሽብርተኞች በአሲምባና በቋራ አሰልጥኖ ያሰማራቸው ኢሕአፓ ነበር ብትልስ ማን አለብህ?? ጌታውን የተማመነ በግ ምን የማያደርገው አለ?

ለመሆኑ እነ ግርማ ከበደ፤ ሻለቃ ብርሃኑ ከበደና መሰሎቻቸው አገር ምድሩን ሲያስለቅሱ የት ነበርክ? አንገቲ ቲራስ ሲር ቀቢሮ ቂጢ ፈንድዶ ነበር? እንዴ ሰጎን! ምነው ምላስህ በነሱ ላይ አይሾርም?

ያንተ ነገር ተወስቶም ማብቂያ የለው! እንኳንም አንተን አልሆንኩ እንጂ እኔ አንተን ብሆን ኖሮ ለጥራዝ መሙያ በሚል ብቻ የፃፍካቸውን ነገሮች ፅፌና አስጠርዤ ለገበያ አልወጣም

ነበር። በጣም አፍር ነበር። እኔ እስከምረዳው ድረስ ማንም ወላጅ ልጆቹን ወደትምህርት ቤት ሲልክ መምህራንን ከራሱ በተሻለ ሁኔታ አይቶና ተንከባክቦ ያሳድግልኛል፤ ያስተምርልኛል ብሎ ነው። አንት ግን ኃፍረት የለህምና እቴጌ መነን የልጃገረዶች ት/ቤት ታስተምር በነበረበት ጊዜ ክፍል ገብተህ ልጃገረዶቹን "ለመሆኑ ምንቸታብሽ ምን ዓይነት ድንጋይ ነው? ብዬ ጠይቅኳቸው" ብለህ መጠየቅህን ትፅፋለህ። ፕርፌሰር ቲቸር እርስዎ ድንጋይ ካሉት እንኳ ምንቸታብሽ ቢ.ኤም.ደብሊዩ ስ ብሆን ምን ሊሆን ነው? ለመሆኑ ስንቷን ልጃገረድ ነው እንዲህ አድርገህ ያጉላልኸው? ስንቷንስ የአዕምሮ ጭንቀት ውስጥ አስገባህ? በእንዲህ ዓይነቱ የማስጨነቅ "ጥበብህ" ስንቷስ ልጃገረድ ትምህርቷን አቋርጣ ቀረች? ስንቷንስ ልጃገረድ አሳስተህ ይሆን? ቤቱ ይቀጠረው። "ሰማያዊውን የኢሠፓ ካኪ ገርግዶና ሽጉጥ ታጥቆ (ደግሞ ሞያ አድርጎት ያንኑ ካኪ ገለጥ እያደረገ ሽንጡ ሊያሳይ ይታገል ነበር) ክፍል እየገባ ለተማሪ 'A+' ና 'A'  አልሰጥም። 'A+' ለማርክስ 'A' የኔ ነው፡ እንዲያው የበረታና አለሁ ያለ ተማሪ 'A' ካገኘ መቼ አነሰው?" ይል የነበረውን ይሉኝታ ቢስ፡ ኃፍረተ ቢስና ቅንጣትም ታህል የሃላፊነት ስሜት ያልነበረው ሌላ ዶ/ር ፕሮፌሰር ተብዬም የምንረሳው አይደለንምና ለታሪክ መዝግበን እናኖረዋለን።

ኢሕአፓንና ያን ትውልድ የምታሸንፍበት እየመሰለህ በየሄድክበት የምታነሳቸው ሆኖም ግን ያንተንና የመሰሎችህን ዕውቀተ-ግልብነት የሚንፀባረቅባቸው ሁለት ጉዳዮች ማርክሲዝም ሌኒንዝምና የብሔር- ጥያቄ ናቸው።

የመጀመሪያውን በሚመለከት ኢሕአፓና አባልቱ ያኔ ገና ያኔ እነ ፀጋዬ ገ/መድህን (ደብተራው)ና ጓዶቹ በጠላት ወያኔ እጅ ከመውደቃቸው ቀደም ብሎ "እንዲህ ያለው ክርክር ውስጥ ተስበን እንኳ አንገባም" ብለው ግልፅ አድርገዋልና እስኪ እኔ አንዳንድ ጥያቄዎች ልጠይቅህ።  ለመሆኑ የትኛው የንድፈ ሃሳቡ አካል ነው እንዲህ አልረዳህ ብሎህ የተቸገርከው?

.የህብረተሰብ ዕድገት ትረካውን? ታዲያ እንዴት ሆኖ ነው ሊቁ፤ የታሪክ ተመራማሪው የምትባለው?

.ፍልስፍናውን? ይሄ ዶ/ር ፕሮፌሰርነት ታዲያ እንዴት ተገኘ? አዳናቂዎችህ የሰጡህ "የክብር" ነገር ከሆነም ይነገረን!

.ምጣኔ ሀብታዊ ትንታኔውን? ዓለም GFC ተብሎ በሚታወቀው ዓለም አቀፍ ምጣኔ ሃብታዊ ቀውስ ውስጥ ተዘፍቆ በነበረበት 2000/2001 ዓም ላይ በአዲስ ነገር ጋዜጣ ላይ " አውሮፓ ቀውሱ በዝቶበት መውጪያ መንገድ ለማግኘት የማርክስን ዳስ-ካፒታል እያነበበ ነው። መፅሐፉ የአውሮፓን ገበያዎች አጣቧል" ብለህ መፃፍህን ታስታውሳለህ? የማርክስ የምጣኔ ሃብት ትንተናዎች ከቀውስ ለመውጫ እየጠቀሙ ነው

ማለትህ  መስሎኝ ነው እኔ የተረዳሁት። ተሳስቻለሁ እንዴ? ስታለምጥ ወይ ያ አድርባይነት የሚሉት ተውሳክ ነው! ለነገሩማ በቅርቡ ያሜሪካው ፕሬዚደንት ባራክ አባማ አዲስ አበባን የጎበኘ ጊዜ በአፍሪካ አዳራሽ ተገኝቶ ለአፍሪካ አምባገነኖች "እናንተ ሃብታሞች ናችሁ፡ ዘርፋችሁ የያዛችሁት ሃብት ይበቃችኋል ወዘተ ወዘተ " ብሎ እንቶ ፈንቶ ንግግሩን አድርጎና የባለሥልጣናትን ዘረፋ "ሕጋዊ" ሽፋን አልብሶት እንደተመለሰ "ፕሬዝዳንት ኦባማ ያፍሪካ መሪዎችን በዘዴ ደቁሰዋቸው ሄዱ" ብለህ አልፃፍከም? ስታለምጥ  ነው ወይስ ያ አድርባይነት የሚሉት ተውሳክ ነው? እንዲያው የግራ ፖሊቲካ ጉዳይ ከተነሳ የኢትዮጵያ ህዝብ ይደነግጣል መስሎህ ነው? ወደ ስዊዘርላንድ ጎራ በልና ተመልከት- አልተርኔቲቭ ሌፍት ፓርቲ ቢሮን ታገኛለህ። ኖርዌይም ከዘለቅህ 21 የፓርላማ መቀመጫዎች ያሉት የግራ ፓርቲ ታገኛለህ። ዜጎቻቸው መብታቸው አልተገደበም።

ምንም አታፍርም - "የብሔር ጥያቄ ሲነሳ እኔ የሰዎችን ጭንቅላት አዞራለሁ" ትላለህ። ችግሩንና የመፍትሔ ሃሳብን በፅሞና ያስቀመጥከበት አንድም ቦታ ግን የለም። እኔ የዋለልኝን መሰረተ ሃሳብና የ ያ ትውልድ ግንዛቤን ተመርኩዤ ትንሽ ልበል።  መጠነኛ ጂኦሜትሪያዊ ዕሳቤ ልጨምርበትም ነው።

የብሔር ጥያቄና መፍትሄው አምባገነኖችና ጥራዝ ነጠቆች አንድ ቀጭን መስመር በቀይ ቀለም አስምረው "ይህችን ቀይ መስመር የተላለፈ ምና ምን" እያሉ የሚሉበት ዋን ዲመንሺናል ጉዳይ አይደለም። ቱ ዲሜንሽናል እንጂ! ዝርግ ወረቀት ያዝና የቀኝና የግራ ጠርዞቹን ተመልከት።  አንዳንድ ወገኖች ቀኝ ጠርዙ ብቻ ይታያቸውና ጥያቄን ያነሳውን ሁሉ "ጠባብ ነህ፤  ተገንጣይ ነህ" እያሉ ቡራ ከረዩ ይላሉ። ሌሎች ደግሞ ግራ ጠርዙ ብቻ ይታያቸውና የብሔር ጥያቄ መፍትሔው ሁሌም መገንጥል ብቻ ነው ብለው ይህን መፍትሔያቸውን ያልተቀበለ ሁሉ "ጨቋኝ ነህ፡ ትምክህተኛ ነህ" እያሉ ከምድረ ገፅ ካላጠፋንህ ይሉታል። ከነዚህ የሁለት ወገን ጽንፈኞች የሚሰማው ጫጫታ ደግሞ አይጣል ነው። ያንተ ዓይነቱ አድርባይ ደግሞ አንዴ ወደአንዱ ጠርዝ ሌላ ጊዜ ወደሌላው ጠርዝ እየተፈናጠረ ያዙኝ ላቀቁኝ ይላል እንጂ የዋለልኝንና የ ያ ትውልድን በነባራዊ ሁኔታዎች ላይ የተመሰረተን የመፍትሔ ሃሳብ በፅሞና እስከዛሬ ሊያዳምጥ አልቻለም፤ አልተዘጋጀምም። ኢሕአፓ ግን ደጋግሞ "እባካችሁ ዝርጉን ወረቀት እያየሁ የማቀርበውን የመፍትሔ ሃሳብ ረጋ ብላችሁ ተመልከቱ" ከማለት የተቆጠበበት ጊዜ የለም። ልብ ካለህ ልብ ብለህ እይ!

ማለቂያ የለውምና ያንተን በዚሁ ላብቃና ወደአሽቃባጮችህ ልሂድና አንድ ሁለቱን ብቻ ላንሳ። አንዱ ክፍሉ ሁሴን የተባለና ከቀድሞ ፅሑፎችህ አንዱ ላይ ትችት ያቀረበና "የሰላ ትችት" አቀረበ ብለህ ልታወድሰው የሞከርከው ሰው ነው። ሌሎቹንማ ምንም ፅሑፎቻቸውን ለገበያ አቅርበህ የተጠቀምክባቸው ቢሆንም እንኳ በአንተ ዕድሜ ካለ ሰው

የማይጠበቅ የስድብ ናዳ አወረድክባቸው። ታምራት ነገራንማ "ወፈፌነቱን ሊያጋባብኝ ሞከረ" አልከው።

አዳፍኔ ገፅ 204 ላይ በከፍተኛ ቃለ-አጋኖ ያዳነቅከው ክፍሉ ሁሴን "ያኔ ነፍስ አውቄ ነበርና ኢሕአፓ መኢሶንን ቀኝ መንገደኛ እያለ ግንባር ግንባሩን ሲለው አስታውሳለሁ ..." ይላል። በቃ አለቀ ደቀቀ። ብቻ ኢሕአፓን የሚኮንን ነገር ይሁን እንጂ የአንተ አንጀት ቅቤ ይጠጣል። ለመሆኑ መኢሶን ቀኝ መንገደኛ እየተባለ የታደነው መቼና በማን ነው? ይህ ሰው እንኳን ያኔ አሁንስ ነፍስ አውቋል?

ሌላው አዳናቂ ደግሞ በየሳምንቱ ሰኞ ሰኞ በእንግሊዝኛ እየፃፈ በአዳናቂ ድረ-ገፆች ላይ ረዥም ፅሑፉ የሚሰራጭለት ሰው ነው። እርሱም መከረኛው ፕሮፌሰር ነውና "መስፍን አዳፍኔ ላይ በፃፈው ሁሉ አልስማማም ያለ ከዚያ ዘለዓለም ከማይቀዘቅዘው ቦታ ይግባ" ሲል ያችኑ "Go to hell" የምትባል የነጮች ዕርግማን ያወርድብናል። ይህ ሰው ባይሆንለት ነው እንጂ ቢሆንለት ኖሮ ሲያል አስገብቶኝ ነበር ማለት ነው። እንዲያው ይህን እንግሊዝኛ የሚችለው እርሱ ብቻ አለመሆኑን ላሳየው "Hey dude! You do not have the slightest idea what the notion of hell is. It is both f****** hot and freezing cold at the same instant. What ever you say, I do not wish you go their " ልል ወደድኩ።

ሰውዬው ውዳሴ መስፍኑን በጣም አብዝቶ "Thank you for all what you tried to do for the *one and only* love of your life, ETHIOPIA" ይላል። (ሰረዝ የኔ)

አጃኢብ ነው! ዓይኔን አታስቁት አለ!

የዛሬ ስንት ዓመት ዋሺንግቶን ፖስት ጋዜጣ እጄ ገብቶ ሳገልብጥ የደረጀ ዴሬሳ ወንድምን ዮናስ ዴሬሳን ፎቶ ተመልክቼ ምን ሊል ነው ብዬ አነባበብኩት። በጋዜጣኛው "ሚስት ለምን አታገባም ተብሎ" ቢጠየቅ "Ethiopia is my wife." ያለው ትዝ አለኝ። እነደረጀ ኢትዮጵያና ህዝቦቿ ለገበያ ቢወጡ ለድለላ ሥራ መሥሪያ ቤት የሚከፍቱ ናቸውና እንዲያ እያሉ ቢቀልዱ ማን አለባቸው? ከምርጫ 97 በኋላ የአዲስ አበባ የማምታቻ ከንባቲ ሆኖ በመለስ ዜናዊ ተሹሞ የነበረው ብርሃኑ ዴሬሳም ይህንኑ ነው ያደረገው። ደላላነት! እና አጫፋሪዎች ረጋ በሉ። እኛ ያለችን አንድና ውድ ኢትዮጵያችን እናታችን ናትና "ሚስቴ" "ፍቅረኛው" እያላችሁ አታላግጡ።

አለበለዚያ *ተስተማረና ተፕሮፌሰረ፤ ተፕሮፌሰረና ተጣፈ!* ይሆናል ነገሩ።